የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ እና ሶሻል ስተዲስ ምዘናዎች
MCAP የውጤት ሪፖርቶችን መረዳት

ከሜሪላንድ የኮሌጅ እና የስራ ዝግጁነት መስፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ (5ኛ እና 8ኛ ክፍል) እና ማህበራዊ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ (8ኛ ክፍል) የሜሪላንድ አጠቃላይ የትምሕርት ችሎታ ግምገማ ፕሮግራም (MCAP) ፈተናዎች በትምህርት አመት 2025–2026 በፀደይ/ስፕሪግ ወቅት ተሰጥተዋል። ለርስዎ ተማሪ ከሚሰጡት የትምህርት አፈጻጸም ምዘናዎች ይሄኛው አንዱ መለኪያ ነው። ከትምህርት ችሎታ ምዘናዎቹ የሚገኙ ውጤቶች፤ ለአስተማሪዎች፣ ለትምህርት ቤት፣ እና ለትምህርት ስርዓቱ የተማሪዎን የአካዳሚክ ብቃት በተመለከተ መረጃ የሚሠጡ ሲሆን፣ ለእርስዎም የተማሪዎን የትምህርት ብቃት ደረጃ ግንዛቤ ይሰጥዎታል። አንድ ተማሪ የአካደሚክ መስፈርቶችን እያሟላ(ች) ስለመሆኑ ግልጽ የሆነ ስዕል ለማግኘት MCAP ውጤቶቹ መታየት ያለባቸው በክፍል ውስጥ ካለው/ካላት የትምህርት ሥራ አፈጻጸም፣ ከሪፖርት ካርድ ውጤቶች፣ እና የመምህር ግብረመልስ ጋር በማገናዘብ ነው።

የእርስዎን ተማሪ የውጤት ሪፖርት እንዴት እንደሚያነቡ

1. **አጠቃላይ ክንውን/አፈጻጸም**–ተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት የሚያገኙት ከአራቱ የትምህርት አፈጻፀም ደረጃዎች በአንዱ ላይ በሚመደበው በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ተመስርቶ ነው። የትምህርት ክንውን/አፈጻጸም ደረጃዎች፡ ተማሪው(ዋ) የትምህርት ብቃት ደረጃን ገና እንዳላሳየ(ች) ከሚያመለክተው ከደረጃ 1 እስከ ከፍል ደረጃ መመዘኛዎች የላቀ የትምህርት ብቃት እንዳሳየ(ች) የሚያመለክት ደረጃ 4 ድረስ ይለያያሉ።

2. **የውጤት ደረጃ** – ይህ ሚዛን የእያንዳንዱን ትምህርት ክንውን የውጤት ደረጃ እና የእርስዎ ተማሪ ከእነዚህ መካከል በየትኛው ደረጃ እንደሚገኝ/እንደምትገኝ ያመለክታል።

3. **ለኮሌጅ እና የሙያ ሥራ ዝግጁነት**– 3 ወይም 4 ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የትምህርት ደረጃ አሟልተዋል ወይም ከማሟላትም የሚበልጥ ስለሆነ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንደተመረቁ የኮሌጅ ደረጃ ኮርስ ለመውሰድ ዝግጁ ናቸው ማለት ነው።

4. **አጠቃላይ የውጤት እርከን ማነፃፀሪያ**–ይሄኛው ክፍል የሚያሳየው በተመሣሣይ የክፍል ደረጃ፣ በተመሣሣይ ት/ቤት፣ በአጠቃላይ በትምህርት ዲስትሪክቱ ዙርያ፣ እና በስቴቱ ውስጥ ካሉት ሌሎቹ ተማሪዎች ጋር ሲመዛዘን የእርስዎ ልጅ በትምህርት መቅሰም ላይ እንዴት እያከናወነ(ች) እንደሆነ ያመለክታል።



የተማሪዎን የውጤት ሪፖርት እንዴት እንደሚያነቡ (የቀጠለ ....)

5. **የማንበብ/የመጻፍ ክንዋኔ** – የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ ሪፖርት የእርስዎን ተማሪ የማንበብ እና የመጻፍ ነጥቦችን ያነፃፅራል። በዚህ ንዑስ ክፍል የሚገኙት ጥያቄዎች ጋር ተማሪዎ ያስመዘገበ(ች)ውን ውጤት በቁጥር ይገልጻል። ለማጣቀሻ ያህል ተማሪዎ ካገኘ(ች)ው የግል ውጤት በተጨማሪ "ከ-እስከ" ውጤት ተገልጿል። ይህኛው ን/ክፍል የት/ቤቱን፣ የዲስትሪክቱን፣ እና የስቴቱን አማካይ ውጤቶች በተጨማሪ ያካትታል።

የውጤት ዝርዝር– የውጤት ሪፖርት በተወሰነ የክህሎት ደረጃ የእርስዎ ልጅ እያቀላጠፈ(ች) ያለውን ወይም ማሻሻል ያለበ(ባ)ትን የተማሪዎን የትምሕርት አፈጻጸም ሁኔታ ያመለክታል። እያንዳንዱ ዝርዝር የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ ተማሪዎች ጋር የእርስዎን ተማሪ የትምህርት አፈጻጸም የሚያሣይ ክብ ማነጻፀሪያ አለው። የሚማርበትን/የምትማርበትን ክፍል የብቃት/የክሂሎት የግንዛቤ ደረጃ የሚገልጽ ውጤት-የሚያሳይ ገለፃም በተጨማሪ ተካትቷል።









የፌደራል ህግ ይደነግጋል።

- ✓ የሜሪላንድ የትምህርት ባለሙያዎች ከትንታኔ አንስቶ ትክክለኛነታቸውን እስከ መገምገም ድረስ እያንዳንዱን ፈተና በማዘጋጀት እና በማሻሻል ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ።
- ✓ የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎች ስሊሚፈቀድላቸው መገልገያዎች እና አኮሞዴሽን በልጆቻቸው IEP ወይም 504 ቡድን አማካይነት ለወላጆቻቸው ሊገለጽላቸዉ ይገባል።
- ✓ በትምህርት አመቱ መጨረሻ የሚሰጡ የትምህርት ውጤቶች የተማሪን የክፍል ደረጃ ትምህርት የግንዛቤ ደረጃ ያመለክታሉ።

የውጤት ሪፖርቶች መምህራን ለቀጣዩ ዓመት የማስተማር እና የተማሪዎችን አቅም የማሳደግ ዕቅድ ለማውጣት፣ እንዲሁም ተማሪዎችን ለቀጣይ የትምህርት ደረጃቸው ለማዘጋጀት የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ናቸው።

- ✓ ቤተሰቦች ስለልጃቸው አካዴሚያዊ ጥንካሬና መሻሻል ስላለበት ሁኔታ ከልጃቸው መምህራንና የት/ቤት ሃላፊዎች ጋር ውይይት ለማድረግ እነዚህን ውጤቶች መጠቀም ይችላሉ።
- ✓ በት/ቤትም ሆነ በመኖርያ ቤት የተማሪን የትምህርት ፍላጎት በይበልጥ እንዴት መደገፍ እንደሚቻል እያንዳንዱን ጉዳይ አብሮ መወሰን ይቻላል።

ከዚህ በታች የሚገኙት ጠቃሚ ድረ-ገጾች ስለሆኑ ይጎብኟቸው!

- ✓ **መልመጃ ፈተና/MCAP Practice Tests**- https://support.mdassessments.com/practice-tests/
- ✓ **የመረጃ ቋት/Achieve**- በየደረጃው የሚገኙ መገልገያዎች/Resources on Standards– https://www.achieve.org/
- ✓ MD State Department of Education- https://marylandpublicschools.org/Pages/Default.aspx
- ✓ **ምርጥ ትምህርት ቤቶች/GreatSchools**- https://www.greatschools.org/gk/common-core-test-guide/
- ✓ **ጎበዝ፣ ጀግና ተማሪ ለመሆን/Be a Learning Hero**- https://bealearninghero.org/learning-tools/skill-builder/